# ማስታወቂያ

## ለኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ነባር ተማሪዎችና በ2013 ለመማር ያመለከታችሁ አመልካቾች በሙሉ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ የትምህርት መርሀ ግብሮች ሲሰጥ የቆየውን የገፅ ለገፅ ትምህርት በዓለም ላይ በተከሰተው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ተቋርጦ የቆየ መሆኑ ይታወሳል፡፡ የተቋረጠውን የገፅ ለገፅ ትምህርት በበይነ መረብ አማካኝነት ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች በመስጠት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርስቲው የ2013 የትምህርት ዘመን በሁሉም የትምህርት መርሀ ግብሮች የሚሰጠውን ትምህርት ለመጀመር ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም

1ኛ፡ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች በበይነ መረብ አማካኝነት ሲሰጥ የነበረውን ትምህርት በማጠቃለል የማጠቃለያ ፈተና ከመስከረም 25 እስከ ጥቅምት 5/2013 ለመደበኛ መርሀ ግብር ተማሪዎች በበይነ መረብ አማካኝነት የሚሰጥ ሲሆን በተከታታይ ትምህርት መርሀ-ግብር ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ ተማሪዎች እንዳስፈላጊነቱ በበይነ መረብ ወይም የጤና ባለሙያዎች ምክር ተግባራዊ በማድረግ በፊት-ለፊት በተመሳሳይ ቀናት ይሰጣል፡፡ ስለሆነም ስትማሩ የቆያችሁ ተማሪዎች በሙሉ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ትምህርት ክፍሉ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ የማጠቃለያ ፈተናውን እንድትወስዱ እናሳስባለን፡፡

2ኛ፡ ለ2013 የትምህርት ዘመን በመደበኛው፤በማታ እና ቅዳሜና እሁድ በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለመማር አስቀድማችሁ የተመዘገባችሁ ዕጩዎች ከጥቅምት 7 እስከ ጥቅምት 9 ቀን 2013 ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የመደበኛ ትምህርት የተመዘገባችሁ ዕጩዎች ስም ዝርዝርና የመለያ ቁጥር በክልላችሁ ወይም በመ/ቤታችሁ በኩል የተላከ ሲሆን በማታ እና ቅዳሜና እሁድ መርሀ ግብሮች ለመማር የተመዘገባችሁ ዕጩዎች ስም ዝርዝር፣ የመለያ ቁጥር፣ የሁሉም ተፈታኞች የመግቢያ ፈተና የጊዜ ሰሌዳና የፈተና አወሳሳድ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ድረ ገጽ **www.ecsu.edu.et** መመልከት ትችላላችሁ፡፡

3ኛ፡የ2013 የት/ት ዘመን የሁሉም ተማሪዎች ምዝገባ በጥቅምት 2013 መጨረሻ ሳምንት አካባቢ ሲሆን፣ምዝገባው እንደሁኔታው በበይነመረብ ወይም በፊት ለፊት የሚካሄድ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

4ኛ፡ የቅድመ ምረቃ ትምህርት የማካካሻ ትምህርትና የማጠቃለያ ፈተና የሚሰጥበት የጊዜ ሰሌዳ በቀጣይ ይገለፃል፡፡

**የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ**